# ግንቦት 7 ለአማራ ክልል ቴሌቭዥን ሰራተኞች ጉቦ እየሰጠ የድርጅቱን ፕሮፖጋንዳ እያሰራ ነው!

(Miky Amhara)

የአማራ ቴሌቪዥን በ2500 ብር ተደልሎ እንኳን የአማራ ህዝብ ጉዳዮችን ሊዘግብ የብአዴንን ስብሰባወች፣ ያካሄዳቸዉን የአመራር ለዉጦች እና ሪፎርሞችን እንዳላየ እያለፋቸዉ ነዉ፡፡ የብአዴንን ጉዳዮች በተቃራኒዉ የአማራ አክቲቪስቶች ናቸዉ እየዘገብን ያለነዉ፡፡ ብአዴን በኢህአዴግ ኮንግረስ ላይ ያነሳቸዉን ሃሳቦች እንዲሁም እንዲሁም የአመራር ምርጫን በተመለከተ እኛ ነን እየዘገብን ያለነዉ፡፡ የአማራ ቴሌቪዥን የክልሉን ብሎም ክልሉን እያስተዳደረ ያለዉን የድሮዉን ብአዴን የአሁኑን አዴፓ የስራ እንቅስቃሴወች እንዲሁም የክልሉን መንግስት እንቅስቃሴ እየዘገበ አይደለም፡፡

የአብንን እማ መቸም አይዘግቡትም፡፡ይህ ደግሞ የተወሰኑ ከ 5 የማይበልጡ ጋዜጠኞች በወር 2500 ብር ከግንቦት ሰባት ስለሚወስዱ ነዉ፡፡ ስማቸዉን ማዉጣት ይቻላል፡፡ ይሄን አይተዉ ካላስተካከሉ እናወጣዋለን፡፡ ጭራሽ ስራ ትተዉ አንተ ገንዘብ እየተቀበልክ ነዉ ይሄን ዘግብ ይሄን አትዘግብ የሚል እስጣ እገባ ዉስጥ ገብተዋል፡፡ በጣም አሳፋሪ ነዉ፡፡ የ50 ሚሊየንን ህዝብ ድርጅት፣ እኛ በምንከፍለዉ ታክስ የሚተዳደር ድርጅት፣ ከብአዴን ተላቀቅ እያልን ስንወተዉተዉ እንዳልከረምን ጭራሽ አሁን ደግሞ የግንቦት ሰባት ልሳን ሁኖ አረፈዉ፡፡

የሶሻል ሚዲያ ፔጁ እማ ሌላ ዜና የለዉም፡፡ ፕሮፌሽናሊዝምን በገንዘብ ለዛዉም በማይረባ ገንዘብ መቀየር ግን ነዉር ነዉ፡፡ ከዛም በላይ ሀገሪቱ እና ክልሉ ዉስጥ ስንት ጉዳይ፣ ስንት መፈናቀል ፣ስንት የኢኮኖሚ እና የፍትህ ጉዳዮች እያሉ የሆነ ፓርቲ ምሳ ተሰባስበዉ ሁሉ ሲበሉ ዜና ማድረግ መዉረድ ነዉ፡፡ያን ያህል በክፉ ቀን ያኮራን ቴሌቪዥን በብጣሽ ገንዘብ አገልግሎትን እንዲህ ያበላሻል፡፡ የአማራ ህዝብ ድምጽ እንድትሆኑ እንጅ የማንም ፓርቲ ድምጽ እንድትሆኑ አይደለም የምንፈልገዉ፡፡